Coptic Orthodox Patriarchate
His Holiness Pope Tawadros II
Pope of Alexandria and
Patriarch of the See of St. Mark
The Papal Center

بطريركية الأقباط الأرثوذكس
قداسة البابا الأنبا تواضروس الثاني
بابا الأسكندرية
وبطريرك الكرازة المرقسية
المقر البابوي

ⲠⲀⲠⲀ ⲀⲂⲂⲀ ⲠⲒⲨⲀⲂ̅
Ⲧⲁⲟⲩⲁⲇⲣⲟⲥ

222 Ramses St., Abbaseya, Cairo, Egypt
222 شارع رمسيس ، العباسية ، القاهرة ، مصر

Tel: 024822580 Fax: 0235365880 email: office@popetawadros.org 0235365880 :فاكس 024822580 :تليفون

*Amharic – Nativity 2024*

**የ2024 ዓ/ምልደት በዓልን በማስመልከት ቅዱስ ፓትርያርኩ ያስተላለፉት ቃለ በረከት**

**በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፣ አሜን።**

የተወደዳችሁ ሆይ፣ እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሳችሁ። እንኳን ለተከበረው የልደት በዓል አደረሳችሁ። ከግብጽ አገር ከሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ አገር እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ። እንኳን ለዚህ ታላቅ በዓል አደረሳችሁ። በግብፅ ውስጥ ባሉ ሁሉም ኮፕቶች ስም የእንኳን አደረሳችሁ መልእክቴን እልካለሁ። በአለም ዙሪያ ላሉ የኮፕቲክ አህጉረ ስብከት እና አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ። አባቶችን እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ፤ ሜትሮፖሊታኖች እና ጳጳሳት፣ እና አባቶች ካህናት፣ ሄጉሜን እና ሽማግሌዎች። የቤተክርስቲያን ቦርዶችን እና ዲያቆናትን እንኳን አደረሳችሁ። በጃንዋሪ 7 ላይ በሚውለው የምስራቃውያን አቆጣጠር መሰረት ገናን ለሚያከብሩ የኮፕቲክ ማኅበረሰብ በሙሉ እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ።

በገና በዓል ላይ የምናስባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ምናልባት ሁላችንንም የሚመለከተን ጠቃሚ ጥያቄ "ክርስቶስ የት አለ?" የሚለው ነው። ዓለም ብዙ አለመረጋጋት፣ ጦርነቶች እና ግጭቶች አሉባት። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ከተወለደ ጀምሮ የሚጠየቀው ጥያቄ "ኢየሱስን የት ነው የምናገኘው?" የሚለው ነው። መልአኩ ለእረኞቹ ተገልጦ "ለሕዝብ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ" ብሏቸው ነበር። ( ሉቃስ 2:10 ) እነሱ በጣም ቀላል ሥራ የሚሠሩ እረኞች ነበሩ። ግን ደግሞ በጎችን እየጠበቁ ነበር፡፡ በረሃ ውስጥ ነበሩ። በሌሊት በጎችን ይጠብቁ ነበር። ከዚያም መልአኩ ይህን ታላቅ ደስታ ሲነግራቸው እነዚህ እረኞች ወደ ግርግም ሄደው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሕፃን በጨርቅ ተጠቅልሎ ሲያዩት እናገኛቸዋለን። ይህ ደስታቸው ነበር። ክርስቶስን ካዩ በኋላ ወደመጡበት ሄዱ። የምስራቅ ጠቢባን ሰብአ ሰገልም ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ እነሱም እንደ መጻሕፍታቸው፣ እውቀታቸውና ስነ ከዋክብት ምርምራቸው ልዩ ባሕርይ ያለው ኮከብ ብቅ ሲል እና ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ሲንቀሳቀስ አይተው አዲስ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ዘንድ ደረሱ፡፡ በመጓዝ ደክመው ደረሱ። ሁላችንም እንደምናውቀው ቀደም ባሉት ጊዜያት የጉዞ ዕድሎች በጣም ውስን ነበሩ። መንገዱ ሳምንታት እና ወራት ወስዶባቸዋል፡፡. በቤተ ልሔም ወደተወለደው ንጉሥ ቤት ደረሱ። አገኙትና ስጦታቸውን ወርቅ፣ እጣንና ከርቤ ሰጡት። ይሄው "የተወለደውን ክርስቶስን ከየት እናገኛለን?" የሚለው ጥያቄ የይሁዳ ንጉሥ ሄሮድስንም አሳስቦታል። ልቡ ግን ክፉ ነበር። ስለዚህ ህፃኑን መፈለግ ወደደ፡፡ ላይ ላዩን እርሱን እንደ ንጉሥ ሊያከብረው እንደሚፈልግ አስመስሎ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ክፋትን ይዞ ነበር። ከዚያም የቤተልሔም ልጆች እንዲገደሉ ያዘዘው ሄሮድስ እንደሆነ ሰምተናል። ልቡ ክፉ ነበር።

"ክርስቶስን የት ነው የምናገኘው?" የሚለው ጥያቄ ገናን ስናከብር ትኩረታችንን የሚስብ ጥያቄ ነው። ምናልባት ክርስቶስን በትልልቅ ቤቶች እና በበለጸጉ ውድ ቦታዎች እንፈልገው ይሆናል። ወይም በሁሉም መልኩ በቴክኖሎጂ ቅንጦት ውስጥ የሚኖሩ ቦታዎች። ወይም በስህተት ክርስቶስ ይኖራል ብለን በምናስብባቸው ቦታዎች። እንደ ቤተ መንግሥቶች እና የቅንጡ ኑሮ የመኖሪያ ቦታዎች። እውነቱ ግን እኛ ባልጠበቅነው ቦታ ክርስቶስን እናገኘዋለን። ምናልባት እንደ ቤተልሔም ያለ ቦታ ውስጥ እናገኘዋለን። እሷ ማንም የማያውቃት፣ ትንሽ እና ስውር መንደር ነች። እሱን በሰው መኖሪያ ሳይሆን በእንስሳት በረት ውስጥ እናገኘዋለን። እርሱ ይኖርበታል ብለን በማንጠብቀው ቦታ እናገኘዋለን። እንዲህ ዓይነቱ ቦታ በቀላልነቱ እና በንጽህናው ተለይቶ ይታወቃል፡ ፡ ስለዚህ ክርስቶስን በምትፈልጉበት ጊዜ በቀላል ቦታዎች እና ንጹህ ቦታዎች ፈልጉት፡፡ ደግሞም በንጽህና፣ ቅድስና እና በየዋህ ህይወት ተለይተው በሚታወቁ ቦታዎች። ክርስቶስን የምናገኘው በደካማ ልቦች ውስጥ ነው። እሱን ፈልጉት። ስለዚህ የተወደዳችሁ፣ ገናን ማክበር ከፈለጋችሁ፣ በዓሉ ስለ አዲስ ልብስ፣ ምግብ፣ የገና ዛፍ እና ብዙ ማስዋቢያዎች ብቻ አይደለም። ይህ አስደሳች አከባበር ነው፤ ይህ ግን በማህበራዊ ደረጃ ላይ ነው፡፡ በመንፈሳዊ ደረጃ፣ ክርስቶስን እና የእሱን ፈለግ መፈለግ አለባችሁ። እሱን ለማየት እና በእርሱ ደስተኛ ለመሆን እሱን ፈልጉት። በእያንዳንዱ ትሑት ልብ ሰው ውስጥ እርሱን ፈልጉት። ሰላምን በሚፈልግ ሰው ውስጥ ሁሉ እርሱን ፈልጉት። ሌሎችን ማገልገል በሚፈልግ ሰው ውስጥ ሁሉ እሱን ፈልጉት። ክርስቶስን ፈልጉ።

አንድ ቀን ከአውስትራሊያ የመጡ ወጣት ወንዶች መጥተው ለማገልገል እንደጠየቁ አስታውሳለሁ። ስለዚህ፣ በአሌክሳንድሪያ አቅራቢያ ወደምትገኝ በሃይራ ጠቅላይ ግዛት ወደምትገኝ አንዲት ትንሽ መንደር ላክኳቸው። ወጣቶቹ የዚህን መንደር አገልግሎታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ የነገሩኝ ብቸኛ አነጋገር “በዚያ ክርስቶስን አገኘነው” የሚል ነበር። ስለዚህ የገና አከባበር የመውሰድ በዓል አይደለም፤ የምትሰጡበት የመስጠት በዓል ነው። ጥረታችሁን፣ ጊዜያችሁን፣ ሀሳባችሁን፣ ገንዘባችሁን እና አገልግሎታችሁን አቅርቡ። በእነዚህም መባዎች ክርስቶስን ታዩታላችሁ። ለራሳችሁ አትኑሩ፤ ብቻችሁን እና በራስ ወዳድነት አትኑሩ። ነገር ግን ለሌሎች ኑሩ። እና ደካማ የሆኑትን ነፍሳት ሁሉ ፈልጉ፡፡ በመከራ፣ በበሽታ ወይም በችግር የሚሠቃዩ ወይም በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ሸክም ያለባቸውን ነፍሳት። ገናን በታህሳስ ወር መጨረሻ የምናከብረው የክርስቶስ ልደት ጊዜ ብቻ አታድርጉት። ክርስቶስን በየቦታው እየፈለጋችሁ ዓመቱን ሙሉ የገና በዓል አድርጉት እንጅ። ውጤቱም ልብን የሚሞላ ታላቅ ደስታን ማግኘት ይሆናል።

የገና ዛፎችን ይሸጥ ስለነበረ አንድ ሰው የሚያምር ታሪክ አስታውሳለሁ፡፡ በገና ዋዜማ የመጨረሻዎቹን ዛፎች ለመሸጥ ሲፈልግ ማንም ሊገዛቸው አልመጣም። ያለ በቂ ገቢ ወደ ቤቱ ሊመለስ በመሆኑ በጣም አዘነ። ምግብ ለማምጣት ወይም ለልጁ ስጦታ ለመስጠት በቂ ገንዘብ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ ሴት ልጁ የገና በአል ሊጠናቀቅ ስለተቃረበ እነዚህን ዛፎች ወስደህ ለሌሎች እንደ ስጦታ ስጥ የሚል ሀሳብ አቀረበችለት። ከዚያም በሚኖርበት ሰፈር ውስጥ አንዳንድ ቤቶችን መምረጥ ጀመረ፡፡ ስለዚህ ወደ መጀመሪያው ቤት ሄዶ አንድ ዛፍ በስጦታ አቀረበ፡፡ የቤቱ ባለቤቶች፣ አንድ ወንድና በጠና የታመመች ሚስቱ፣ እሱን ተቀበሉት። በዚያ ዛፍ በጣም ተደሰቱ። ከዚያም ዛፍ ሊሰጥ ወደ ሁለተኛው ቤት ሄደ። በዚህ ቤት ውስጥ ያለችው እናት ልጇን አጥታለች፡፡ እሷ በጣም ስላዘነች ገናን ማክበር አልፈለገችም ነበር፡. ዛፉን በስጦታ ሲሰጣት የገና ደስታዋ ተመለሰ። ከዚያም ዛፍ ሊሰጣቸው ወደ ሦስተኛው ቤት ሄደ። ባልና ሚስት ሲጨቃጨቁ  እና ሚስት ልትፋታ ቀርባ አገኛቸው። ዛፉን ሲያቀርብ በዛፉ ተደሰቱ፤ በገናም ደስ አላቸው። የዚህ ሂደት ውብ ውጤቱ ባልየው ከታመመ ሚስቱ ጋር በነበረበት የመጀመሪያ ቤት ውስጥ ደስታቸውን ለመግለጽ ፈለጉ፤ ስለዚህ ለዚህ ሰው ምግብ አቀረቡ፡፡ ከዚያም ትንሽ ቆይቶ በሁለተኛው ቤት ውስጥ ልጇን በሞት ያጣችው እናት ደስታዋን ለመግለጽ እና ስጦታ ለመስጠት ፈለገች፡፡ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለየችው ልጇ ሹራብ እየሠራች ነበር። እናም ሹራቡን ወስዳ ለሰውየው በስጦታ ሰጠችው። ስለዚህ አባትየው ወስዶ ለሴት ልጁ ስጦታ አድርጎ ሰጣት። ሊፋታ የነበረው ሦስተኛው ቤተሰብ የገና ዛፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ ባልና ሚስቱ ራሳቸውን መገምገም ጀመሩ እና የፍቺ ወረቀቶችን ቀደዱ። ሰላምም በዚህ ቤት አደረ። ከታረቁ በኋላ ለዚህ ሰው ስጦታ አቀረቡ። ይህ ሰው እና ሴት ልጁ በምግቡ እና ስጦታዎች በጣም ተደሰቱ። ይህ ነበር የገና ደስታቸው።

ይህንን መልእክት ስልክላችሁ ደስተኛ ነኝ። ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እና አድባራት። በዚህ የገና በዓል አከባበር ላይ በዚህ መልእክት በመገናኘታችን ደስተኛ ነኝ። በዚህ በገና በዓል እና በአዲሱ ዓመት መጀመሪያ ላይ ልባችሁን የሚሞላ ደስታ እና ሐሴትን ለእናንተ እመኛለሁ። ለሁላችሁም፣ ለመላው አብያተ ክርስቲያናት፣ አህጉረ ስብከት፣ እና ገዳማት፣ እንዲሁም ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እና ሰሚናሪዎች በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን አደረሳችሁ እላለሁ። በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱሱ ቤተሰብ ጉብኝት ከተባረከች ከግብፅ ምድር ይህን የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት እልክላችኋለሁ። በኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ባነበብናቸው ትንቢቶች የተባረከች ናት። በሐዋርያው ቅዱስ ማርቆስ ስብከትም ተባርካለች። እግዚአብሔር ይጠብቃችሁ፤ ከእናንተ ጋርም ይሁን። መልካም አዲስ አመት፤ መልካም የልደት በዓል።

Tawadros II